# ክፍል አንድ

## ዓለመ መላእክት፡

እግዚአብሔር መላእክትን በከተማ አስር በነገድ መቶ አድርጎ ከፈጠራቸው በኋላ ተሰወረባቸው:: እነርሱም "ፈጣሪያችን ማን ይሆን?" እያሉ ይጠይቁ ጀመር:: በዚህ ጊዜ በክብር ላቀ ብሎ ይገኝ የነበረው ሣጥናኤል "እኔ ነኝ የፈጠርኳችሁ" በማለቱ ክርክር ተነስቶ መላእክት ለሁለት ተከፈሉ:: በመጨረሻም እግዚአብሔር አምላክ ተገልጦላቸው አቡሀ ለሐሰት (የሐሰት አባት) ሣጥናኤልንና ሠራዊቱን ወደ ዘለዓለም ፍርድ፣ ባሉበት የጸኑትን ቅዱሳን መላእክትን ደግሞ የዘለዓለም ሕይወትና ክብር ሰጣቸው:: በዚህም መላእክት ከእግዚአብሔር አምላክ ጋር ግንኙነት ጀመሩ:: ራዕ. 12÷78፣ ኢሳ. 14÷15::

# ክፍል ሁለት

በብሉይ ዘመን የነበሩ ደጋግ አባቶች ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ግንኙነት በ4 ይከፈላል:: እነሱም የተነሱባቸው ዘመናት:-

1. ዘመነ አበው
2. ዘመነ መሳፍንት
3. ዘመነ ነገሥት
4. ዘመነ ነቢያት /ካህናት/ ናቸው::

## ምዕራፍ አንድ

## ዘመነ አበው

ሕገ ልቡና እየተባለም ይጠራል:: ይህ ዘመን ሰዎች በሕገ ልቡና ይመሩበት የነበረ ዘመን ሲሆን እግዚአብሔርም በልቡናቸው ባስቀመጠላቸው ሕግ ይመሩ ከነበሩት አበው ጋር የነበረው መንፈሳዊ ግንኙነት ስለሆነ ዘመነ አበው፣ የሕገ ልቡና ዘመን ይባላል::

ከአዳም እስከ ኖኅ ያለው 2,256 ዓ.ዓ. ሲሆን ከኖኅ እስከ ሙሴ ያለው 1,600 ዓመት ከአዳም እስከ ሙሴ ያለው 3,856 ዓ.ዓ. ነው:: በዚህ ዘመን ከነበሩት አበው መካከል ዓበይቱን እንመለከታለን::

### ሀ. አዳም :-

- 🕮 ከመሬት የተፈጠረ ያማረ ማለት ነው::
- 🕮 በዕለተ ዓርብ ኤልዳ በምትባል ሀገር /በማዕከለ ምድር በቀራንዮ/ በአርአያ ሥላሴ ተፈጠረ:: ዘፍ.1÷27፣ ኩፋሌ 5÷6::

እግዚአብሔር አርብ በነግህ በእኛ አምሳል በእኛ አርአያ ሰውን እንፍጠር ብሏል። ዘፍ.1÷26 ይህንንም ሳውርያኖስ ሲተረጉም ከፍጥረቱ ሁሉ ስሙ ይበልጣል። ከሁሉ የሚበልጥ ሰውም ከአብ ብቻ የተፈጠረ አይደለም ከሦስቱ ተ ፈጠረ እንጂ እኛን አስመስለን ሰውን እንፍጠር ብሏልና። አብ እኔ ልፍጠር አላለም፣ ወልድንም አንተ ፍጠር አላለውም፣ መንፈስ ቅዱስንም ይፍጠር አላለም እንፍጠር ብሏል እንጂ። ወልድን ወይም መንፈስ ቅዱስን አንተ ፍጠር ብሎት ቢሆን አንዱ የአንዱ ታዛዥ እንደሆነ ባስረዳ ነበር።

በሦስት አካላት መካከል አንዱ በአንዱ የማይታዘዝ መሆኑን ለማስረዳት የመታዘዝን ነገር ለማራቅ በክብር አንድ እንደሆኑ ሲገልጹ ምሳሌ በሌለት በአንዲት ፈቃድ እንፍጠር ብሏል። እንፍጠር ማለት የሦስትነት እኛን አስመሰለን አንድ ሰው እንፍጠር ማለት ግን የአንድነት አነጋገር ነው ። ሰው በአብ አምሳል ብቻ ተፈጠረ ብለው ሰዎች እንዳይጠራጠሩ አይደለም በሦስቱ ስም በመጠመቅ ከበረ እንጂ ጥንቱን በሦስቱ አምሳል ተፈጥሮ ነበርና። ማቴ. 28÷19.

🕮 ለአዳም ረዳት ትሆነው ዘንድ ሔዋን ተፈጠረች። ዘፍ.2÷21፣ 1ኛ ቆሮ.11÷9።

🕮 አዳም ከተፈጠረበት ምድር በአርባ ቀኑ፣ ሔዋን በተፈጠረች በሰማንያ ቀን ወደ ገነት ገቡ ዘፍ.2÷8፣ ኩፋሌ 4÷17።

## ገነት የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት

- በገነት ልዩ ልምላሜ እንዳለ ሁሉ በቤተክርስቲያን ልምላሜ ጽድቅ አለ። በተጨማሪም በቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ያሉ ወይራዎች ፣ ጽዶች፣ ባሕር ዛፎችና የመሣሠሉት ዕፀዋት ሁሉ ያለ ምክንያት አልተቀመጡም ። ቤተክርስቲያን የገነት ምሳሌ ስለሆነች ነው። ዕፀዋቱን ስንመለከት ልምላሜ ገነትን እንድናስብ ያደርገናል።
- በገነት ደስታ እንጂ ሀዘን እንደሌለ በቤተክርስቲያንም ደስታ መንፈሳዊ አለ። በንስሐ በደላችን ሲደመሰስ፣ በክርስቶስ ሥጋና ደም ስንቀደስ፣ ጋብቻችን በተክሊል ስንፈጽም ሕይወታችን በመዓዛ መንፈስ ቅዱስ ይረካል። ሀዘናችን በደስታ ይለወጣል። መንፈሳዊ ሰው ላዩ የጠወለገ ይመስላል እንጂ ውስጡ ግን በእግዚአብሔር ሰላም ደስተኛ ነው። መዝ 63 ፥10

🕮 7 ዓመት ከ2 ወር ከ17 ቀን በኋላ እባብ አሳታቸው፤ ከገነትም ተባ ረሩ። ዘፍ.3÷1፣ ኩፋሌ 4÷17።

🕮 አጋንንትም አዳምንና ሄዋን ምንም ሳይበድሉት እነሱ ከማይገቡባት ከገነት በማስወጣት ለሚከተሉት የመከራ ዓይነት ዳረጓቸዋል።

1. ተባርከው የነበሩት ተረገሙ
2. ተሰጥተው ተቀሙ
3. ተከብረው ተዋረዱ
4. ለብሰው ተራቆቱ
5. ሕይወታቸውን በሞት ለወጡ።

- 🕮 ከገነት ከወጡ በኋላ በደብረ ቅዱስ ይኖሩ ነበር።
- 🕮 በንስሐ በመጸጸታቸው፣ በመመለሳቸው እንደ ዲያብሎስ ወድቀው ሳይቀሩ የድኅነት ቃል ኪዳን ተቀበሉ። ዘፍ.3÷15-22። የዚያን ጊዜ የቤተክርስቲያን መሠረት ተጣለ። ለዚህም ነው ስለ ቤተክርስቲያን ባነሳን ቁጥር የመጀመሪያው ሰው አዳም ሁልጊዜ ትዝ የሚለን።
- 🕮 አዳም 930 ዓመት ሲሆነው ሞተ።

**ጥያቄ:-**

1. ሰው ፈጣሪውን በምን በምን ይመስለዋል?
2. እግዚአብሔር በገነት ስንት ዕፆችን አኖረ ? ምን ምን ይባላሉ?
3. እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ ሁለት ሁለት አድርጐ ሲፈጥራቸው አዳምን ግን ብቻውን ነው የፈጠረው ለምን?
4. አዳም ስንት ልጆችን ወልዷል ?
5. ከአዳም ምን እንማራለን ?
6. ከአዳም ጐን ሔዋን መገኘቷና ለአዳምም አንድ ሔዋን ብቻ እግዚአብሔር መፍጠሩ ምን እንማርበታለን?

## ለ. አቤልና ቃየል:-

የአዳምና የሔዋን ልጆች ናቸው። ዘፍ.4÷1-17።

- ✞ የቃየል መንትያ ሉድ፣ የአቤል መንትያ አቅሌማ ይባላሉ።
- ✞ ከወላጆቻቸው በትውፊት በተማሩት መሠረት መሥዋዕት አቀረቡ።
- ✞ እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት ተቀበለ። ዘፍ. 4÷4።
- ✞ ቃየል አቤልን ገደለው። ሞትም በአቤል ተጀመረ።

## ሐ. ሄኖክ :-

- ◆ የያሬድ ልጅ ነው። ዘፍ. 5÷18።
- ◆ ከአዳም ጀምሮ 7ኛ ትውልድ ነበረ። ይሁዳ 4÷14።
- ◆ በእምነቱ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘው ተመስክሮለታል። ዕብ. 11÷5።
- አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ በሥጋ ሞትን ሳያይ ከዚህ ዓለም ተለየ። ዘፍ. 5÷24።
- ስለዚህም በአቤል ሞት እንዲታወቅ በሄኖክም ሕይወት /ዘለዓለማዊነት/ የተረዳ ሆነ።
- ሰባት ዓመት በእግረ ገነት በብሕትውና ነበረ። አንድ መጽሐፍ የጻፈ ሲሆን ስለጌታችን መገለጥና ስለ ኖኅ ዘመን ጥፋት ተንብየዋል።

መ. ኖኅ:-

- የአዳም ልጅ የሴት ትውልድ ነው:: ዘፍ. 5÷28::
- ክፉ ሕዝብ በነበረበት በዚያ ዘመን ኖኅ ብቻ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ:: ዘፍ. 6÷9::
- 500 ዘመን ከሆነው በኋላ ሴምን፣ ካምን፣ ያፌትን ወለደ:: ዘፍ. 5÷32::
- እግዚአብሔር የጥፋትን ውኃ በምድር ላይ እንደሚያመጣ አስጠነቀቀው:: ኖኅና ቤተሰቦቹ እንዲሁም ሕያው ነፍስ ካላቸው ተ ባእትና አንስት ፍጥረታት /ከሚበሉት ሰባት ሰባት ከማይበሉት ሁለት ሁለት/ የሚድኑበትን መርከብ እንዲያዘጋጅ ታዘዘ:: ዘፍ. 6÷13-22::
- 600 ዓመት በሆነው ጊዜ የውኃ ጥፋት መጣ:: ከርሱ ጋር ወደ መርከቡ ከገቡት በቀር የዳነ አልነበረም:: ዘፍ. 7÷1::
- እግዚአብሔር ስለ ኖኅ የጥፋትን ውኃ ከምድር አደረቀ:: ኖኅም ወጥቶ መሥዋዕትን ሰዋ:: እግዚአብሔርም ምድርን ዳግመኛ በጥፋት ውኃ እንዳያጠፋ ከኖኅና ከሕያው ፍጥረት ሁሉ ጋር ቃል ኪዳን ገባ:: ምልክቱም ቀስተ ደመና ነበረ:: ዘፍ.8፣ ዘፍ.9÷8-12:: ልጆቹንም ብዙ ተ ባዙ ብሎ ባረካቸው::
- ኖኅ ወይን ተከለ፣ ከወይን ጠጁም ጠጥቶ ሰከረ:: ካምም ያባቱን ነውር ገለጠ:: በዚህም ልጁ ከነዓን ተረገመበት ይህን ያላደረጉት ሴምና ያፌት ተባረኩ:: ዘፍ.9÷20-27::
- ልጆቹም ምድርን ሲከፋፈሉ የካም ልጅ ኩሽ /ኢትዮጲስ/ እንዲሁም ልጆቹ ሳባና አቢስ ዕጣ የደረሳቸው ቦታ የኢትዮጵያ ምድር ነበረች::
- 950 ዓመት ሲሆነው ሞተ:: ዘፍ. 9÷29::
- ኖኅ የሠራት መርከብ ፍጥረታትን ከጥፋት ማዳኗ ለቤተክርስቲያንና ለእመቤታችን ምሳሌ ናት::

## የኖኅ መርከብ

የኖኅ መርከብ በውስጧ የነበሩትን ሁሉ ለአርባ መዓልት እና ለአርባ ሌሊት ከሠማይ ይወርድ ከምድር ይፈልቅ ከነበረው የጥፋት ውኃ አድናለች:: ቅድስት ቤተክርስቲያንም በክርስቶስ አምነው ወደ እርስዋ የገቡትን ከኃጢአት ፣ ከሞተ ነፍስ ታድናቸዋለችና::

- ከመርከቧ ውስጥ የነበሩት ሲድኑ ከመርከቧ ውጭ የነበሩት በጥፋት ውኃ ተደምስሰዋል:: በክርስቶስ አምነው ወደ ቤተክርስቲያን የገቡ ከዘለዓለማዊ መቅሰፍት ይድናሉ፤ በክርስቶስ አምነው ወደ ቤተክርስቲያን ያልገቡ ግን የመዳን ተስፋ የላቸውም ዮሐ 6፥35-37:: ማቴ 11፥28

- የኖኅ መርከብ በውስጧ ሦስት ክፍል ነበራት ቤተክርስቲያንም ሦስት ክፍል አላት ቅኔ ማህሌት፣መቅደስ፣ቅድስት ናቸው::
- ኖኅ በሦስቱ ክፍል ውስጥ ከበድ ያሉትን በታች ፣ቀለል ያሉትን ከላይ፣ እርሱና ልጆቹ በመካከል ተቀምጠዋል ይህም፣ በቤተመቅደስ ካህናት በቅድስት ንስሐ የገቡ ሥጋወደሙ የተቀበሉ ምዕመናን በቅኔ ማኅሌት ሃይማኖትን በንዑስ ክርስቲያንነት ገና ደጅ የሚጠኑ ምዕመናን በየደረጃቸው ለመቆማቸው ምሳሌ

ቤተክርስቲያን ከኖኅ መርከብ ትበልጣለች የኖኅ መርከብ ያዳነችው ከሞተ ሥጋ ነው ቤተክርስቲያን ግን ከሞተ ነፍስ ታድናለች

### ጥያቄ:-

1. ለሰው ልጅ መትቶ መግደል ያስተማረ ማን ነው?
2. በኖኅ የሳቀበት ካም ሆኖ ሳለ የረገመው ከነዓንን ነው ለምን?
3. ከኖኅ ምን እንማራለን?
4. «የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደሆነ አዩ:: ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶች ለራሳቸው ወሰዱ » ዘፍ. 6÷2 የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት እነማን ናቸው? የሰው ልጆችስ?
5. ቤተክርስቲያን ከኖኅ መርከብ ትበልጣለች እንዴት?

### ሠ. አብርሃም:-

- የታራ ታላቅ ልጅ ነው፣ የቀድሞ ስሙ አብራም ነበር::
- አባቱ ታራ ጣኦት አምላኪ ነበር:: እግዚአብሔርም አብርሃምን ከሀገሩ እንዲወጣ ከዘመዶቹ ተለይቶ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ አባቶች የመጀመሪያው ይሆን ዘንድ ከትውልድ ሀገሩ ከዑር እንዲወጣ አነጋገ ረው:: ዘፍ. 12÷1::
- በሚስቱ በሣራ ፈቃድ ከግብፃዊት ገረዱ ከአጋር እስማኤልን ወለደ:: ዘፍ.16÷1-4:: ቃል ኪዳንና ምልክት የሆነውን ግዝረት ከሰጠው በኋላ የተስፋው ልጅ ይስሐቅ ከሣራ ተወለደለት:: ዘፍ.17÷21::
- በእግዚአብሔርና በአብርሃም መካከል ቃል ኪዳን ተደረገ፤ ምልክቱም ግዝረት ነበር:: ዘፍ.17÷2-4፣ ቆላ.2÷8-13::
- እግዚአብሔር በመምሬ አድባር ዛፍ ተገልጦለት ልጅ እንደሚወልድ ነገ ረው:: ዘፍ.18÷1-25 ዘሩም በይስሐቅ ዘር እንደሚጠራለት ተነገረው:: ዘፍ. 21÷12-13::
- እግዚአብሔር ልጁን ይስሐቅን ይሠዋለት ዘንድ አዘዘው:: ዘፍ. 21÷1-18::

* «የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» ተብሎ ነበር:: ዘፀ. 12÷1::
* በ175 ዓመቱ ሞተና በኬብሮን ተቀበረ:: ዘፍ. 25÷9 እና 10::

**ጥያቄ:-**

1. የአብርሃም ድንኳን የእመቤታችን ምሣሌ ናት እንዴት?
2. የአብርሃም ድንኳን የቤተክርስቲያን ምሣሌ ናት እንዴት?
3. ይስሐቅ ሊሰዋባት የነበረች የሞሪያም ተራራ የቤተክርስቲያን ምሣሌ ናት እንዴት?

## ረ. ይስሐቅ:-

- የስሙ ትርጓሜ ይስቃል ማለት ነው::
- የአብርሃምና የሣራ ልጅ ሲሆን የያዕቆብም አባት ነው::
- ሣራ በእርጅናዋ ወለደችው:: ዘፍ.17÷15-21፣ 18÷9-15፣ 21÷1-7፤
- አባቱ ለመሥዋዕትነት አቀረበው:: ዘፍ. 22::
- ከጸለየ በኋላ ከሚስቱ ከርብቃ ኤሳውንና ያዕቆብን ወለደ:: ዘፍ. 25÷19-21::
- እግዚአብሔር የአብርሃምን ተስፋ አጸናለት:: ዘፍ. 26÷35 ባረከውም:: ዘፍ. 26÷12-14፣ 28፣ 29 ልጆቹንም ባረካቸው:: ዘፍ.35÷28-29::

## ሰ. ያዕቆብ

* ተረከዝን ይይዛል ማለት ነው::
* ርብቃ ለይስሐቅ ከወለደችለት መንታዎች ትንሹ የ12ቱ የእስራኤል ሕዝብ ነገዶች አባት ነው:: ዘፍ. 25÷27-34::
* የኤሳውን ብኩርና ገዛ:: ዘፍ. 25÷33፣ ዘፍ. 27 የብኩርናንም በረከት አገኘ::
* ከኤሳው ለማምለጥ ሚስቱንም ለማግኘት ወደ እናቱ ወንድም ወደ ላባ ሄደ:: ዘፍ. 27÷32፣ 28÷9 የመሰላልንም ሕልም አየ:: የአብርሃምም ተስፋ ተሰጠው :: ዘፍ. 27÷20-22::
* 20 ዓመት ለላባ አገልግሎ ልያንና ራሔልን አገባ፤ ብዙ ከብትም አገኘ:: ብዙ ልጆችንም ወለደ:: እነዚህም የአሥራ ሁለቱ (12ቱ) ቤት እስራኤል አለቆች ሲሆኑ እነርሱም:-

| | | |
|---|---|---|
| 1. ሮቤል | 5. ዳን | 9. ይሳኮር |
| 2. ስምኦን | 6. ንፍታሌም | 10.ዛብሎን |
| 3. ሌዊ | 7. ጋድ | 11. ዮሴፍ |
| 4. ይሁዳ | 8. አሶር | 12. ብንያም ናቸው:: |

- እግዚአብሔር በጵንኤል ዘፍ.32÷22-32፣ በቤቴል ዘፍ.35÷9-15 ተገለጠለት:: ስሙንም እስራኤል ብሎ ሰየመው::
- ብዙ ዓመትም በከነዓን ከኖረ በኋላ በረሃብ ጊዜ ወደ ግብፅ ተሰደደ:: ዘፍ.33÷18፣ 46÷47::
- ትንቢት እየተናገረ የዮሴፍን ልጆችና የራሱን 12 ልጆች ከባረከ በኋላ በ147 ዓመቱ ሞተ:: ዘፍ.47÷27፣ 49÷33::
- በአብርሃም መቃብርም ተቀበረ:: ዘፍ. 50::

<u>የያዕቆብ ልጆች:-</u>

| ከልያ የተወለዱ | ከራሔል አገልጋይ /ባላ/ |
|---|---|
| 1.ሮቤል/ዘፍ.29÷32፣ሉቃሴ10÷24፣20÷32 | 1. ዳን. /ዘፍ. 30÷6/ |
| 2. ስምዖን /ዘፍ.29÷33፣ ኩፋሌ 20÷26/ | 2. ንፍታሌም /ዘፍ.30÷8፣ ኩፋሌ 20÷33/ |
| 3. ሌዊ /ዘፍ.29÷34፣ ኩፋሌ 20÷27/ | <u>ከልያ አገልጋይ /ዘለፋ/</u> |
| 4. ይሁዳ /ዘፍ.29÷35፣ ኩፋሌ 20÷28/ | 1. ጋድ /ዘፍ.30÷11፣ ኩፋሌ 20÷34 |
| 5. ይሳኮር /ዘፍ.30÷18፣ ኩፋሌ 20÷36/ | 2. አሴር /ዘፍ.30÷13፣ ኩፋሌ 20÷35/ |
| 6. ዛብሎን /ዘፍ.30÷20፣ ኩፋሌ 20÷37/ | ከራሔል |
| 7. ዲና /ዘፍ.30÷21፣ ኩፋሌ 20÷37/ | 1. ዮሴፍ /ዘፍ.30÷22፣ ኩፋሌ 20÷38/ |
| | 2. ብንያም /ዘፍ. 35÷16-18፣ኩፋሌ 23÷34/ |

## ሸ. <u>ዮሴፍ:-</u>

ከያዕቆብ 12 ልጆች መካከል ዮሴፍ ከራሔል የተወለደ የመጀመሪያ ልጅ ነው:: ዘፍ.30÷20-24:: ከጠባዩ መልካምነትና ከዝናው፣ ከፈጸመው ትልቅ ሥራ የተነሣ ከሁሉም ልጆች የከበረ ሆነ:: አባቱ በተለይ ወደደው:: ሕልሞችም ስላለመና ስለ ወንድሞቹ መጥፎ ወሬ ስለአወራ ጠልተው ሸጡት:: ዘፍ.37÷1 በግብፅ ባሪያ ሆኖ ሳለ በጲጥፋራ ቤት ለአስተዳዳሪነት ተሾመ:: የጲጥፋራ ሚስት ግን በተንኮል እና በሐሰት አሳሰረችው:: ከዚያም ሞገስን አግኝቶ በግዞት ቤት አለቃ ሆነ:: ዘፍ.40÷41::

- ለሰባት ዓመታት እህልን በመሰብሰቡ ብዙ ሰዎችንና ቤተሰቡን ከሞት አዳነ:: ዘፍ.42÷45፣ 47÷13-2/
- ግብጻዊት አግብቶ ኤፍሬምንና ምናሴን ወለደ:: ዘፍ. 42÷50-51 አባቱንና ወንድሞቹን ወደ ግብፅ አስመጥቶ መገባቸው::

✞ በወንድሞቹ ቂም አልያዘም / ዘፍ. 50÷15-22/
✞ ከእስራኤል ነገዶች የሁለቱ አባት ሆነ፡፡ ያዕቆብም ብኩርናውን ለዮሴፍ ይሁን በማለት የዮሴፍን ልጆች ባረከ፡፡ በስሞቻቸው ነገደ ኤፍሬምና ነገደ ምናሴ ተብለው ተጠሩ፡፡ዘፍ.48፣ 2ኛ ዜና 5÷1፣ ዘኁ.1÷49፣ ዘዳ.33÷15-17፡፡

ማጠቃለያ፡- በዘመነ አበው የነበሩ 22ቱ አበው የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. አዳም | 7. ሄኖክ | 13. ሳላ | 19. ታራ |
| 2. ሴት | 8. ማቱሳላ | 14. ዔቦር | 20. አብርሃም |
| 3. ሄኖስ | 9. ላሜሕ | 15. ፋሌቅ | 21. ይስሐቅ |
| 4. ቃይናን | 10. ኖኅ | 16. ረግው | 22. ያዕቆብ /1ኛ ዜና. 1÷1-27/ |
| 5. መላልኤል | 11. ሴም | 17. ሴሮሕ | |
| 6. ያሬድ | 12. አርፋክሳድ | 18. ናኮር | |

## ምዕራፍ ሁለት
## ዘመነ መሳፍንት

መስፍን ማለት ገዢ ወይም ዳኛ ማለት ነው፡፡ በእስራኤል ነገሥታት ማስተዳደር ከመጀመራቸው በፊት ሀገሪቱን ከጠላት ወራሪ የሚያድን፣ የንጉሥ ዘር የሌለው ሰው ነው፡፡ በተለይም ቤተ እስራኤል ወደ ሀገራቸው ከገቡና ኢያሱ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔርን ትተው የአሕዛብን አማልክት በማምለክ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ እየሠሩ እግዚአብሔርን ያስቆጡት ነበር፡፡ እርሱም ሊመልሳቸው ብሎ ለሚማርኳቸው ወራሪዎች አሳልፎ ይሰጣቸው ነበር፡፡ ወራሪ በመጣ ቁጥርም እስራኤል ተጨንቀው ተጸጽተው ወደ እግዚአብሔር ይጮሁ ይጸልዩ ነበር፡፡ እርሱም ይመራቸውና መሳፍንት እያስነሳ ከሚማርኳቸው እጅ ያድናቸው ነበር፡፡ እስራኤልን መሳፍንት ያስተዳድሩበት የነበረው ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ከ1644 እስከ 1083 ዓመት /ከ3856-4417 ዓ.ዓ./ ያለው ጊዜ ዘመነ መሳፍንት ይባላል፡፡ በመሳፍንት ግን የተዳኙት ለ450 ዘመን ነበር፡፡ የሐዋ. 13÷20

**በዚህም ዘመን እስራኤልን ያስተዳደሩ 17 መሳፍንት ነበሩ፡፡**

| | |
|---|---|
| 1. ሙሴ | 10. ኢያዕር /መሳ. 10÷3-5/ |
| 2. ኢያሱ | 11. ዮፍታሔ /መሳ. 1÷11/ |
| 3. ጎቶንያል /መሳ. 3÷12-30/ | 12. ኢብፃን /መሳ. 12÷8-10/ |